# አዲስ የዕድገት አቅጣጫን ያመላከተ ዕለት

**ቴዎድሮስ ተካልኝ**

11-22-14

ዘጠነኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን የህዳሴው ግድብ በሚገነባበት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መዲና በሆነችው አሶሳ ከተማ በደማቅ ህብረ-ብሔራዊ ቅኝት ሊካሄድ የቀሩት የጥቂት ሳምንታት ዕድሜ ብቻ ነው። ይህን የሀገራችን ህዝቦች በጋራ ፈቃዳቸው አብረው በመተሳሰር አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመገንባት ቃል የገቡበትን ዕለት ልዩ የሚያደርገው በዓሉ የሚከበርበት ታላቁ የህዳሴ ግድብ በሚገነባበት ክልል ውስጥ የሚከበር መሆኑ ነው።

ሁሉም የሀገራችን ህዝቦች ግድቡን ለመገንባት አሻራቸውን ባላቸው አቅም ሁሉ እያሳረፉ ባሉበት በአሁኑ ወቅት ለበዓሉ የላቀ ድምቀት እንደሚሰጠው አያጠራጥርም። ይህም የሀገራችን ህዝቦች አንድም፣ ብዙም ሆነው ለህዳሴያቸው መረጋገጥ ያላቸውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ይመስለኛል።

ሁላችንም እንደምናውቀው በብዝኃነት ላይ መሠረቱን የጣለው ይህ የሀገራችን ህዝቦች አንድነት ለህዳሴውም ስኬት መገለጫ በመሆኑ የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ህገ መንግሥት ጠብቆ ለማቆየት ዜጎች በጽናት ዘብ ቆመዋል፡፡

እናም የሀገራችንን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ያስተሳሰረው የጋራ አስተሳሰብ ሲታወስ፣ በቅድመ ፌዴራል ኢትዮጵያ በገዥዎች ሰፍነው የነበሩ የተዛቡ ግንኙነቶችን ብቻ ሳይሆን ዜጎች  የፈጠሯቸውን ገንቢ ትስስሮች ጭምርንም ማውሳት የሚያስፈልግ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ለዛሬው ማንነታችን መነሻ እስሾዎች በመሆናቸው ትናንትን በዛሬ መነጽር ማየት ስለሚገባ ነው።

እርግጥ ያለፉት ዘውዳዊው የጨለማና የወታደራዊው አምባገነን ዘመናት ከተወገዱ በኋላ የተዛቡ ግንኙነቶችን በማስተካከል ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባትና ገንቢ እሴቶችን ለማስፋት ምሶሶ ሆኖ የሚያገለግለው ህገ መንግሥት የፀደቀበት ቀንንም

ማውሳት ያስፈልጋል፡፡ ይህም የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን አዲሱ የኢትዮጵያዊነት ማንነት ዘላቂነቱ እንዲረጋገጥ መከወን ያለብንን ጉዳይ እንድናስብ ማድረጉ አይቀሬ ነው፡፡

ከዚህም ጋር ብዝኃነታችንን አክብረንና ጠብቀን እንድንኖር ብሎም የጋራ ቤታችንን በጋራ አቅማችን እንድንገነባ በድጋሚ ቃል የምንገባበት ነው፡፡ ምን ይህ ብቻ! አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የሚገነባው ብዝኃነትን ተቀብለን በእኩልነትና በአንድነት በሚደረግ ርብርብ መሆኑንም ያረጋግጥልናል፡፡

በመሆኑም በዚህ ፅሑፌ በኢትዮጵያ እየተገነባ ያለውን ሕብረ ብሔራዊ ፌዴራል ሥርዓት መነሻ አስተሳሰቦችና ልዩ ባህሪያትን በመዳሰስ፤ ከሌሎች አገሮች ፌዴሬሽኖች ጋር የሚጋሯቸውን ተመሣሣይ መገለጫዎቹንም ለመቃኘት እሞክራለሁ፡፡

በቅድሚያ ግን "ፌዴራል" ለሚለው ቃል የዘርፉ ምሁራን ከሚሰጡት ትርጓሜ እንነሳ፡፡ "ፌዴራል" የሚለው ቃል "ፌደስ" ከሚለው የላቲን ቃል የተወረሰ ነው፡፡ ቃሉ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ሕብረትን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ነው፡፡ ትርጉሙም "ቃል ኪዳን" ወይም አብሮነትና በጋራ የመኖር ውልን ይወክላል፡፡

ፌዴሬሽኖች ቃሉ ሕብረታቸውንና የመንግሥታቸውን ቅርጽ ለመግለጽ ይጠቀሙበታል፡፡ በመሆኑም ፌዴራላዊ ሥርዓት ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ መንግሥታት የሚፈጥሩት የራስ አስተዳደርና የጋራ አስተዳደርን ያጣመረ በቃል ኪዳን የሚመሠረትና በአጋርነት የሚመራ ሥርዓተ መንግሥት ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ሁሉም ፌዴሬሽኖች የተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎች የድርድር ውጤቶች መሆናቸውን ነው፡፡

በመሆኑም እያንዳንዱ ፌዴሬሽን ከታሪካዊ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዝምድናዎች የወረሳቸውና በምሥረታው ወቅት ከነበረው ነባራዊ ሁኔታ የሚመነጩ ልዩ ባህሪያት አሉት፡፡ ልዩ ባህሪያቶቹም አንዱ ፌዴሬሽን ከሌላው ፌዴሬሽን የተለየ ገጽታ እንዲኖረው ያደርጋሉ፡፡

እያንዳንዱ ፌዴሬሽን ያሉት ማንነቶችና የባህል ልዩነቶች ብዛት፣ በመጠቅለል ወይም ሥልጣን ወደ ታች በማውረድ የተመሠረተ ፌዴሬሽን መሆን አለመሆኑ፣ የፌዴሬሽኑ

አባል ክልሎች ብዛት፣ ጂኦግራፊያዊ ሥፋትና በፌዴራሉ ህገ መንግሥት የሚሰጣቸው የእውቅና ደረጃ፣ የታክስና ፋይናንስ ክፍፍል፣ ክልሎች በዓለም አቀፍ ግንኙነት ላይ ያላቸው ተሳትፎ፣ የህገ መንግሥት ማሻሻያ ሥርዓት፣ ያልተማከለ አስተዳደር ደረጃ የሚሉት ጉዳዩች የልዩነት መገለጫዎች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

እነዚህ ልዩነቶች በመኖራቸው ምክንያት ለሁሉም ፌዴሬሽኖች የሚስማማ ወጥ አወቃቀርና የሥልጣን ክፍፍል አለመኖሩን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ፌዴራላዊ ሥርዓተ መንግሥታትን የሚያመሳስሉና ከሌሎች የመንግሥት አወቃቀር ዓይነቶች የተለዩ የሚያደርጓቸው የጋራ ባህሪያትም አሏቸው፡፡

ከዚህ ፅንሰ ሀሳብ መነሻነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሥርዓተ መንግሥት ከሌሎች አገራት ፌዴሬሽኖች የሚጋራቸው የጋራ መገለጫዎች እና የሚለዩት የራሱ የሆኑ ባህሪያት አሉት፡፡የኢትዮጵያ ህብረ ብሔራዊ ፌዴራል ሥርዓት አንዱ መሠረታዊ መነሻ አስተሳሰብ ወይም እምነት ለረዥም ዓመታት በኢትዮጵያ ሰፍኖ የነበረውን የተዛባ የሕዝቦች ግንኙነት በማስተካከል አዲስ የኢትዮጵያዊነት ሕብርና ዝምድና መመሥረቱ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከ80 በላይ የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ያቀፈች አገር ነች፡፡ እነዚህ ማንነቶች ባለፉት የዘውድና ወታደራዊ አገዛዝ ዘመናት ማንነታቸውን እንዲሸሽጉ አሊያም ጨርሰው እንዲፍቁ የተገደዱበት ሥርዓቶች ነበሩ፡፡ በነገሥታቱ ዘመን የኢትዮጵያዊነት መለኪያ የራስ ማንነትን በመተው የገዥዎችን ቋንቋ መጠቀም፣ ባህልና ኃይማኖትን መከተል፣ ገዥዎቹ የደገፉትን መቀበልና መስሎ መታየትን ነበር፡፡

በሰሜን ኢትዮጵያ ለም መሬት በመኳንንትና በገዥዎች አገልጋዮች የተያዘ ስለነበር ገበሬዎች ሙሉ በሙሉ ከመሬት ባለቤትነት ባይነቀሉም የመሣፍንቱን መሬት በማልማትና ሀብት በመሰብሰብ አገልጋዮች እንዲሆኑ ተደርገው ነበር፡፡ በደቡብ ኢትዮጵያ ደግሞ የማንነት ጭቆና የአካባቢዎቹ ሕዝቦች የሀብት ምንጭ የሆነውን መሬታቸውን ሙሉ በሙሉ ከመንጠቅ ጋር ተያይዞ የተፈፀመ እንደነበር አይዘነጋም፡፡

በመሣፍንታዊ ሥርዓተ መንግሥት "አንድ አገር" የመፍጠርና የማቃናት ሂደት፣ "አንድ ቋንቋ፣ ባህል፣ ኃይማኖትና  አገር" በሚል ፍልስፍና ማንነትን በማፈን

የተከናወነ ሆኖ ከኢኮኖሚ ጭቆና ጋር በማስተሳሰር የተፈፀመ ነበር፡፡ በነገሥታት ዘመን ሌሎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችም የማይታሰቡ ነበር፡፡ የሥርዓቱን ፍፁማዊነት ለመግለጽ "ንጉስ አይከሰስ፤ ሰማይ አይታረስ" በሚል ተረት ይገለጽ ሁሉ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡

ዘውዳዊውን ሥርዓት ተክቶ የመጣው የደርግ አስተዳደር በዘውድ ዘመን የነበረውን የማንነት አፈናና የኢኮኖሚ ጭቆና አጠናክሮ ቀጥሎበታል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነታቸውን ለማስከበር በአፄው ዘመን የጀመሩትን ትግል ለማጥፋት አስከፊ ጭፍጨፋ ፈፅሟል፡፡ ማንነትን የማስከበርና እኩልነትን የማረጋገጥ የመብት ጥያቄዎችን በሠላማዊ መንገድ ማንሳት ይቅርና ማሰብ በራሱ የሕይወት ዋጋን ያስከፍላል፡፡

ደርግ በዘውድ ዘመን የነበረውን የአንድ ኃይማኖት የበላይነት በመሠረቱ ሳይቀይር ነገር ግን ለውጥ ያመጣ በማስመሰል ሁሉም ኃይማኖቶች እምነታቸውን በነፃ እንዳያራምዱ አፍኗል፤ የኃይማኖት ተቋማትን ዘግቷል፤ በርካታ አማኞች አገራቸውን ጥለው እንዲሰደዱ አስገድዷል፡፡

ደርግ የዘውዳዊው አገዛዝ የኢኮኖሚ ምንጭ የነበረውን መሬት በመንጠቅ የመሣፍንታዊ ሥርዓት መሠረት እንዲነቀል አድርጓል፡፡ ይሁንና ለገበሬዎች ያከፋፈለው መሬት ግን ፍትሃዊነት የጎደለው ነበር፡፡

አርሶ አደሮች ምርታቸውን በገበያ ዋጋ እንዳይሸጡ የዋጋና የኮታ ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት፤ ሀብታቸውን፣ ጉልበታቸውንና እውቀታቸውን አሟጠው ለተሻለ ምርታማነት እንዳይሰሩና ኑሯቸውን እንዳይለውጡ ነፃነታቸውን ያፈነ ሥርዓት ነበር – ደርግ፡፡

ባለፉት የዘውድና የወታደራዊ አገዛዝ ዘመናት ዜጎች ማንነታቸው የታፈነበት፤ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ተቆጥረው በአገራዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ድምጽ ማሰማት የተነፈጉበት፤ ተሹመው በሚመጡ ባለሥልጣናት እንዲተዳደሩ የተገደዱበት – ኢትዮጵያ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እሥር ቤት የሆነችበት ዘመናት ነበሩ፡፡

የኢትዮጵያ ሕብረ ብሄራዊ ፌዴራል ሥርዐት የተመሠረተበት አንዱ መሠረታዊ አስተሳሰብ ያለፉት መንግሥታት የፈጠሯቸውን የተዛቡ ግንኙነቶችን ማስተካከል ነው የሚባለውም ያለምክንያት አይደለም፡፡

ይህም ሲባል በዋነኛነት የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የኃይማኖቶች እኩልነትን ማረጋገጥ ነው፡፡ ዜጎች ቋንቋቸው፣ ባህሎቻቸው፣ ታሪኮቻቸውና የማንነት መገለጫዎቻቸውን እንዲያስፋፉና እንዲያሳድጉ የሚያስችላቸው እኩል እድል መፍጠር ማለት ነው፡፡

ያለፉት ሥርዓቶች በሕዝቦች መካከል የፈጠሩት ጥርጣሬና መራራቅን በማስወገድ ኢትዮጵያ ሁሉም ማንነቶች እኩል የሚስተናገዱባት የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቤተሰብ እንድትሆን በዓይነቱ የተለየ ግንኙነት እንዲፈጠር ማድረግ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከታሪካቸው የወረሱትን በጎ ትስስር በማጎልበት በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አዲስ የሕዝቦች ግንኙነት መፍጠር ከፌዴራላዊ ሥርዓቱ መሠረታዊ አስተሳሰቦች አንዱ ነው፡፡ ኢትዮጵያን በአዲስ የግንኙነት መሠረት የመገንባት ጉዳይ የሁሉም ማንነቶች የጋራ እቅድ ነውና፡፡

ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአገራዊ አጀንዳዎች ላይ የመወሰን ሥልጣንና ኃላፊነት እንዲኖራቸው በማድረግ በኢትዮጵያ እድገትና ሥልጣኔ ላይ እንዲረባረቡ የሚያስችላቸው ምህዳር መፍጠርም ያስፈልጋል፡፡

ይህ ዓይነቱ አዲስ ግንኙነት ኢትዮጵያን በፅኑ መሠረት ላይ ለመገንባት የሚያስችል ሰፊ አቅምና ጠንካራ ጉልበት እንዲኖር ያስችላል፡፡ የጋራ አስተዳደር የተፈጠረበት አንዱ መነሻ እምነትም ሁሉም ማንነቶች የኢትዮጵያ ባለቤቶች ለማድረግ ነው፡፡

እንዲሁም ማንነቶች በአካባቢ ጉዳዮችና እነሱን በሚመለከቱ አጀንዳዎች ላይ ወሳኞቹ እንዲሆኑ ማድረግ አንዱ መሠረታዊ እምነት ነው፡፡ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የእለት ተእለት አኗኗራቸውንና የወደፊት ሕይወታቸውን በሚወስኑ አጀንዳዎች ላይ የሚወስንላቸው ከላይ የሚጫን ኃይል እንዳይኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ይህንን እውን ማድረግ ማለት "አንድ ቋንቋ፣ ባህል፣ ኃይማኖት" የሚለውን ያለፉት ገዥዎች ሌጋሲ ለማስወገድ ያስችላል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በጉዳዮቻቸው ላይ ባይተዋር የሆኑበትን የተዛባ ግንኙነት በማስቀረት ከአካባቢያዊ አጀንዳ ተነስተው ለአገር ግንባታ የሚበጁ በጎ ሀሳቦች እንዲያመነጩ የሚያስችል አስተሳሰብ ነው፡፡

ዜጎች በልማት አጀንዳ ተሳታፊ ስላልነበሩ ህይወታቸውን የሚለውጥ ሀብት የማፍራትና ከአገሪቱ ሀብት በፍትሃዊነት የመጠቀም መብት አልነበራቸውም፡፡ የሕብረ ብሄራዊ ፌዴራል ሥርዓቱ አንዱ መሠረታዊ እምነት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የሀብት ምንጭ የሆነውን መሬት ባለቤቶች እንዲሆኑ ማድረግ፣ የጋራ አስተዳደር ማለትም ፌዴራል መንግሥት ከሚያከናውናቸው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማቶችና ከሚሰበሰበው ሀብት ተመጣጣኝ ጥቅም እንዲያገኙ ማስቻል ብሎም በተጎናፀፉት የራስ አስተዳደር አማካይነት አቅማቸውን አስተባብረው አካባቢያቸውን እንዲያለሙ ሥልጣንና ኃላፊነት መስጠት ነው፡፡

ባለፉት መንግሥታት በአገሪቱ ተንሰራፍቶ የኖረውን የተዛባ ግንኙነት በመፋቅ አዲስ ኢትዮጵያዊ ማንነት ለመገንባት የሚያስችሉ የማንነቶች እኩልነት ማረጋገጥ፣ ሁሉም ዜጎች ኢትዮጵያን በመገንባት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ፣ በአካባቢ ጉዳዮቻቸው ላይ ወሳኝ የሚሆኑበትን የራስ አስተዳደር ማረጋገጥ በአጠቃላይ ከአገሪቱ ልማት ተመጣጣኝ ጥቅም እንዲያገኙ ማድረግ ሕብረ ብሄራዊ ፌዴራል ሥርዓቱ የተነሳበት ዋናው መሠረታዊ አስተሳሰብ ነው፡፡

ሌላው ዐቢይ ቁም ነገር ደግሞ የሁሉም አገራት ፌዴሬሽኖች ሁለት ምክር ቤቶች ያሏቸው መሆኑ ነው፡፡ የተወካዮች ምክር ቤት 'አንደኛ ምክር ቤት ወይም የታችኛው ምክር ቤት' በሚል የሚታወቅ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ 'የላይኛው ምክር ቤት ወይም ሁለተኛ ምክር ቤት' በሚል ይገለፃል፡፡ ሁለተኛው ምክር ቤት በካናዳ ሰኔት፣ በአሜሪካ የላይኛው ቻምበር ወይም ሰኔት፣ በጀርመን ቡንደስራት፣ በሕንድ ራጅያ ሣባህ ወይም የክልሎች ካውንስል፣ በደቡብ አፍሪካ ብሔራዊ የክልሎች ምክር ቤት፣ በኢትዮጵያ ደግሞ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ተብሎ ይጠራል፡፡ ሥልጣናቸውም እንደየአገራቱ ሁኔታ ይለያያል፡፡

የኢትዮጵያ ሕብረ ብሄራዊ ፌዴራል ሥርዓት ልዩ ባህሪያት የሚባሉት ያለፉ የተዛቡ ግንኙነቶችን ለማስተካከል የተደነገጉ የአገሪቱን ተጨባጭ ኅብረተሰባዊ መዋቅሮች የሚያንፀባርቁ ወይም ሕብረ ብሄራዊ ፌዴራል ሥርዓቱን አወቃቀር የሚወስኑ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግሥት የሰፈሩ የሥርዓቱ ልዩ ባህሪያት የመነጩበት አስተሳሰብ የሕዝብ ልዕልና ወይም የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ልዕልና መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ባለፉት የዘውድና ወታደራዊ አገዛዝ ዘመናት በአገራቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ የተቆጠሩበት ፍፁም ፀረ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶችን አሳልፈዋል፡፡ የወቅቱ ገዥዎችና አገልጋዮቻቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ዕድል ለመወሰን የተቀመጡ አምባነገኖች ነበሩ፡፡ ከአዲሲቷ ኢትዮጵያ የሚጠበቅ አንድ መሠረታዊ ጉዳዮ የጥቂቶችን ልዕልና ያሰፈነውን ያለፈውን ሌጋሲ በማስወገድ የሕዝቦችን ልዕልና ማረጋገጥ ነው፡፡

አገሪቱ የምትመራባቸው መሠረታዊ መርሆዎች፣ ፖሊሲዎችና ሕጎች የሚመነጩት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፍላጎቶችን ለማሟላት በመሆኑ እያንዳንዱ የመንግሥት እንቅስቃሴ ከዚህ አንፃር ይቃኛል፡፡ የመንግሥት ሥልጣን፣ መንግሥት የሚያራምዳቸው እምነቶች፣ የሚከተላቸው መርሆዎችና ፓሊሲዎች ምንጭ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ናቸው፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ሥርዓቱ ልዩ ባህሪያት የአወቃቀር መልኮች፣ የሥልጣን ክፍፍልና ትስስር መሠረታዊ መነሻ የሕዝብ ልዕልና ነው የሚባለውም ለዚሁ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የፌዴራል ሥርዓቱ አባል መንግሥታት የተደራጁት በመሠረቱ በብሔር ብሔረሰብ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ባለፈው ታሪክ ማንነቶች የተነፈጉትን መብት፣ ታፍኖ የነበረውን ታሪክ፣ ቋንቋ፣ ባህልንና ሌሎች የማንነት መገለጫዎች በህገ መንግሥት ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ተፈፃሚ ማድረግ የሚችሉት ይህንኑ አወቃቀር በመከተል ስለሆነ ነው፡፡

ማንነቶች የተዛባውን ግንኙነት መወገዱን ማረጋገጫ መሣሪያ እንደሆነ ስላመኑበትና በዚህ አወቃቀር አዲስ የእኩልነት ግንኙነትና የጋር ህልውና እንዲመሠረት ስለወሰኑ የተከተሉት አወቃቀር ነው፡፡

ይህ ነው የኢትዮጵያ ፌዴራል ሥርዓት አንዱ ልዩ ባህሪ ተደርጎ የሚወሰደው፡፡ ባደጉት አገራት በተለምዶ የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት ተደርገው የሚወሰዱት ሕዝቦች ናቸው፡፡ ይህ አስተሳሰብ የቡድን መብቶችን ወደ ጎን መተውን ብዙዎች ምሁራን ይስማሙበታል፡፡

ከዚህ ባሻገር ግን የኢትዮጵያን ሁኔታ ስንመለከት የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት ዜጎች ናቸው ብሎ ማለፍ በቡድን ማንነቶች ሲነሱ የነበሩ ተጨባጭ የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ሊመልስ የሚችል አልነበረም፡፡ በአፋኝ ሥርዓቶች ሥር ሆነው ማንነታቸውን ላለማጣት በተለያዩ ወቅቶችና ደረጃ እየታገሉ ያሳለፉ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት ዜጎች ናቸው የሚል ድንጋጌ ሊቀበሉ አይችሉም ነበር፡፡

የአዲሲቷን ኢትዮጵያ የወደፊት ዕድል የመወሰን ሥልጣን ባለቤት መሆን እንዳለባቸው በወኪሎቻቸው አማካይነት ይፋ አድርገዋል፡፡ በምሥረታው ወቅት የገቡትን ቃል በአፈፃፀም ሂደት እንዳይዛነፍ የመጠበቅ ኃላፊነት የሚሰጣቸውን ህገ መንግሥት የመተርጎም ሥልጣን ወስደዋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ቁልፍ ትርጉም በመከባበር፤ በመተማመንና በመተባበር በእኩልነት አብሮ የመኖር ስምምነት ነው፡፡

የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት የግል መብቶችን ለማረጋገጥ ወሣኝ እንደሆነ የመንግሥታቱ ድርጅት የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ ይገልፃል፡፡ ብዙ ፀሐፊዎች የቡድን መብቶች ከግል መብቶች ተለይተው መገደብ የሌለባቸው እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡

የግል መብቶችን በማረጋገጥ ብቻ የቡድን መብቶችን ማረጋገጥ እንደማይችል፣ የቡድን መብቶችን የሚከለክል ሥርዓት የግለሰብ መብቶችን ብቻ በማስከበር የተሟላ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊሆን እንደማይችል ይከራከራሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ያደጉ የዴሞክራሲ አገሮች የቡድን መብቶችን በተሟላ መልኩ ባለመረጋገጣቸው ምክንያት የቡድን መብት ጥያቄዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከሩ የአገራቱን ውስጣዊ ሠላም በማናጋት ላይ ይገኛሉ፡፡ የኢትዮጵያን ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ የብሔሮችና ብሔረሰቦች እሥር ቤት ልትሆን የቻለችው የቡድን ማንነቶች ማፈን ዋነኛ የጭቆና መገለጫ ስለነበር ነው፡፡

ይህን ጭቆና በትግል በማስወገድ የራስ አስተዳደር መብትን በማረጋገጥ ብቻ የሚመለስ አልነበረም፡፡ ህገ መንግሥቱን በማፅደቅ ሂደት ሲነሱ የነበሩ ጥያቄዎችና ክርክሮች ይህንን ግልፅ ያደርጋሉ፡፡

የአንዳንድ ብሔሮች የፖለቲካ ድርጅቶች ከጅምሩ የመገንጠል ጥያቄ አንስተዋል፤ አንዳንዶች ደግሞ ነባሩ የተዛባ ግንኙነት በፈጠረባቸው ሥነ ልቦናዊ ጫና ምክንያት በሰንደቅ ዓላማ ቀለማት አመራረጥ ሳይቀር በስፋት ተከራክረዋል፡፡

ይህ የሚያመለክተው ከመገንጠል በመለስ ያለውን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ማረጋገጥ ለብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በእርግጥ የሚያረካ እንዳልነበረ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ካለፉት 23 ዓመታት ተጨባጭ ተሞክሮ የምንረዳው ጉዳይ የመገንጠል መብት የብሔርና ተጓዳኝ ጭቆናዎችን ለማስወገድ ዋስትና ተደርጎ እንደታየ፤ ይህ መብት በህገ መንግሥት ከተደነገገ በኋላ ጥያቄውን ሲያነሱ የነበሩ ኃይሎች በህብረቱ መቀጠል መቻላቸውን ነው፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ፌዴራል ሥርዓት አንዱ ልዩ ባህሪው የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት በማረጋገጥ ህብረትን ማስቀጠል መቻሉን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራል ሥርዓት የአመሠራረት ሂደት ሁለት ባህሪያት ያካተተ ነው፡፡ የደርግ ሥርዓት እንደተወገደ የነበሩና ቀጥሎ የተፈጠሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በመሠረቱ በብሔራዊ ማንነት የተደራጁ ሆነው የያዟቸው ዓላማዎችና ፍላጎቶች የተራራቁ ነበሩ፡፡

የአመሠራረቱ ሂደትም እነዚህን የተራራቁ ፍላጎቶች የነበሯቸው የፖለቲካ ኃይሎች ተቀራርበውና ተሰባስበው በህብረቱ እንዲቀጥሉ የተስማሙበት፤ የሥርዓቱ ባለቤትነት፤ ቅርፁና መሠረታዊ መርሆዎቹ በድርድርና በስምምነት የወሰኑበት ሂደት ነበር፡፡

የሥልጣን ክፍፍሉ በድርድርና በስምምነት ሲወሰን ማዕከላዊ መንግሥት እንዲኖርና ሥልጣኑም በህገ መንግሥቱ የተዘረዘረውን እንዲሆን የወሰኑት የብሔሮችና ብሔረሰቦች ተወካይ የፖለቲካ ኃይሎች ናቸው፡፡

ሌላው የፌዴራል ሥርዓቶች አወቃቀር ልምዶች እንደሚያመለክቱት ለሕብረቱ አባላት ሥልጣን የሚከፋፈሉባቸው ዘዴዎች ተለይተው የተሰጡ፣ የጋራና ቀሪ ሥልጣኖች ተብለው ይታወቃሉ፡፡

ነፃ የነበሩ መንግሥታት በድርድር አንድን የጋራ ሕብረት ወይም ፌዴሬሽን ሲመሰርቱ ቀሪ ሥልጣኖች የክልሎች እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡ በኢትዮጵያ የሥልጣን ክፍፍሉን የወሰኑ ኃይሎች ነፃ መንግሥታት የነበሩ ባይሆኑም ቀሪ ሥልጣኖች የክልሎች እንዲሆኑ አድርገዋል፡፡

እነዚህ ምክንያቶች የሚያሳዩት አዲሱን ሕብረት የመሠረቱ ኃይሎች ከዳር ወደ ማዕከል በመሰባሰብ ፌዴሬሽኑን የመሠረቱ መሆናቸውን ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ያኔ በኢትዮጵያ ቀድመው ህልውናቸውን ያረጋገጡ መንግሥታት ስላልነበሩ ሥልጣን ከላይ ወደ ታች በማውረድ የተመሠረተ ሕብረት እንደሆነ የሚያሳይ ባህሪ አለው፡፡ እነዚህ የሥርዓቱ ባህሪያት በምሥረታው ወቅት ከነበሩ የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታዎች የመነጩና አገሪቱን ከማፈራረስ ያዳነ ሥርዓት እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡

ሌላው ጉዳይ በኢትዮጵያ የሚገኙ ኃይማኖቶች በተለያዩ ወቅቶች ከውጭ የገቡ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ኃይማኖቶች ተቻችለውና ተከባብረው ለመኖር የነበራቸው ፍላጐት ብዙ ፈተና ገጥሞታል፡፡

በተለያዩ ወቅቶች የነበሩ ነገሥታትና ሱልጣኖች አንዱ በሌላው ላይ የበላይነትን ለመቀዳጀት ሲሉ በእምነቶች መካከል ግጭቶችና ጦርነቶችን ይቀሰቅሱ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በርካታ ቤተክርስቲያናትና መስጂዶች ወድመዋል፤ ብዙ አማኞች ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡ በደርግ ጊዜም ሁሉም ኃይማኖቶች እምነታቸውን በነጻነት እንዳያራምዱ ታፍነዋል፡፡

ሆኖም እነዚህ እምነቶች ዘመን ተሻጋሪ የመቻቻል፣ መከባበር መደጋገፍ ታሪክ አሳልፈዋል፡፡ የገዥዎችን የተሳሳተ የኃይማኖት ፖሊሲና ቅስቀሳ ወደ ጐን በመተው አንድ ኃይማኖት ከውጭ ሲመጣ በሠላም ተቀብለውና አስተናግደው እንዲኖሩ አድርገዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ኃይማኖቶችን ተገን ያደረጉና ከእምነቶቹ መርህ ውጭ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች በቀሰቀሷቸው ግጭቶች ምክንያት የወደሙ የኃይማኖት ተቋማትን በጋር እየገነቡ መጥተዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያ የኃይማኖቶች የመቻቻል፣ የመከባበርና የመደጋገፍ ተምሣሌት ተደርጋ የምትወሰድ አገር ነች፡፡

በኢ.ፌዴሪ ህገ መንግሥት ከተደነገጉ የሕዝቦች መብቶች አንዱ የኃይማኖት እኩልነት ነው፡፡ መንግሥትና ኃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን፤ ሁሉም ሰዎች በመካከላቸው የዘር፣ የብሔር፣ የብሔረሰብ፣ የጾታ፣ የኃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ እኩል የሕግ ጥበቃ እንደሚደረግላቸው፣ ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የሕሊናና የኃይማኖት ነጻነት፣ የመረጠውን ኃይማኖት ወይም እምነት ለብቻው ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን የማምለክ፣ የማስተማርና የመግለጽ መብት እንዳለው ህገ መንግሥቱ ደንግጓል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግሥት ለእነዚህ ድንጋጌዎች ልዩ ትርጉም የሚሰጣቸው የኃይማኖቶች እኩልነትና የእምነት ነጻነት ሳይረጋገጥ ያለፈውን የተዛባ ግንኙነት ማስተካከል አይቻልም ከሚል መሠረታዊ አስተሳሰብ በመነሳት ነው፡፡

አዲስ የኢትዮጵያዊነት ማንነት የመገንባት ጉዳይም ከእነዚህ መብቶች ጋር በቀጥታ የተቆራኘ ነውና፡፡ ሌላው ነጥብ ለሕዝብ የሚገደብ መብት መኖር የለበትም የሚል መሠረታዊ እምነት ስላለ ጭምር ነው፡፡

የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በግልም ይሁን በቡድን የመረጡትን እምነት የመከተል መብታቸውን ማረጋገጥ የሕዝብ ልዕልና አንድ አካል ስለሆነ ነው፡፡ ስለሆነም መከባበርና መደጋገፍ ሁሉም የእምነት ተቋማት ሊከተሏቸውና በአማኞቻቸው ላይ ሊገነቧቸው የሚገቡ እሴቶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

በዚህ እምነትና አስተሳሰብ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ዛሬ እጅ ለእጅ ተያይዘው የህዳሴ ጉዟቸውን ቀጥለዋል፡፡ ትሩፋታቸው የሆነውን ታላቁን የህዳሴ ግድብ ይቃኛሉ። እንደጀመሩት እንደሚጨርሱት ቢያውቁም ቅሉ በታላቁ መሪ አቶ መለስ ዜናዊ የተበረከተላቸውን ዋንጫ ይዘው ዳግም ቃል ይገባሉ።

እናም በዓሉን በአሶሳ ሲያከብሩ ይበልጥ የሚጠብቃቸው የደመቀ ህብረ-ብሔራዊነት እንዲሁም በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተው አንድነት ከብረት የጠነከረ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል። ከፊት ለፊታቸው ወደ አዲስ የዕድገት አቅጣጫ የሚወስዳቸው አዲስና ብሩህ የተስፋ ቀን ይጠብቃቸዋልና። እርግጥም ህዳር 29 ሃያል ዕለት ነው–አዲስና በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ የዕድገት አቅጣጫን ያመላከተ ቀን ነውና።